

# ሆዱን ያየ ሆዱን ተወጋ

*ይህ: ግጥም፡ለሆዳቸው: ሲሉ: ህሊናቸውን:በቆራጥነት: ለገበሩ: ወንድምና: እህቶች: መታሰቢያ: ይሁን::*

ህዳሴ:ህዳሴ: ብሎ: ለፈለፈ:

ምድረ ሆዳም ሁሉ አሰፈሰፈ

ፍርፋሪ አገኝ ብሎ አነፈነፈ

ከዘረኞች ጋራ ባንዴ ተሰለፈ::

ስማ ሆዳሜ የአገር ሸክም:

ያገኘህ መስሎህ ጥቅማ ጥቅም

አትሯሯጥ አትቀላውጥ

ሀገር ህዝብህን አትሸጥ::

ህዳሴ ህዳሴ ብለው ሲነግሩህ

በደደቢት ቋንቋ ሲያጭበረብሩህ

አንተም አመነሃቸው እውነት መስሎህ

ተከትለህ ስትሮጥ ትንፋሽ እስኪያጥርህ

ትንሽ ባገኝ ብለህ ከሚዘረፈው

የህዝቡን መበደል ከደህ አረፍከው::

ታሪክህ ሲነገር ይኸ ዘመን አልፎ

የክህደትህ መጠን አያልቅም ተጽፎ::

ተው ተመለስ እባክህ ጊዜው ሳይረፍድ ብዙ

ለሆድ ብሎ ማደር ትልቅ ነው መዘዙ

ለትውልድ ይተርፋል ሸክሙና ጓዙ::

ታዛቢ